# የምዕዐቱ የምሥራች

ቅፅ 64 ቁጥር 3(759) "እግዚአብሔር የመንግሥታት ሁሉ ገዥ ነው።" (መዝሙረ ዳዊት 113፥4)

## ጌታ እግዚአብሔርና መንግሥታት

በዚህች ምድር ላይ የሚቋቋምና ሥልጣን የሚይዝ መንግሥት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀና ያለእግዚአብሔር ፈቃድም ሊቆም እንደማይችል ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጣል (ሮሜ 13፥1)።

እግዚአብሔር የእርሱ ለሆነው ሕዝብ ንጉስና ገዥ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ንጉስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው በሕዝቡ ጥያቄና ፍላጎት ነበር። «ንጉሥ ይሁንልን እኛም ደግሞ እንደ አሕዛብ እንሆናለን፤ ንጉሣችንም ይፈርድልናል፤ በፊታችንም ወጥቶ ስለእኛ ይዋጋል አሉት። ሳሙኤልም የሕዝቡን ቃል ሁሉ ሰማ ለእግዚአብሔርም ተናገረ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን «ቃላቸውን ስማ ንጉሥም አንግሥላቸው አለው»። ሳሙኤልም የእስራኤልን ሰዎች እያንዳንዳችሁ ወደከተማችሁ ሂዱ አላቸው» (መፅሐፈ ቀዳማዊ ሳሙኤል 8፥20)

ንጉሥ ሳኦል የእግዚአብሔር ሕዝብ የመጀመሪያው ንጉሥ ሆኖ በተመረጠበት ዘመን ፍልስጤማውያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገዳደሩበትና የሚያጠቁበት ዘመን ነበር።

የእግዚአብሔር ሕግጋትና ትዕዛዛት የተፃፉበት የእግዚአብሔር ታቦት ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በሚቆምበት ጊዜ ታላቅ ድልና ታምራት ይገኝ ነበር። (መፅሐፈ ሳሙኤል ካልእ 5-6)

የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶችም ከእግዚአብሔር ታቦት ክብርና ሞገስ የተነሳ በፍርሃትና በጭንቀት ይዋጡ ነበር። «ፍልስጤማውያንም ፈርተው እግዚአብሔር ወደ ሰፈር መጥቷል አሉ። ደግሞም እንዲህ አሉ ወዮልን ከዚህ አስቀድሞ እንዲህ ያለ ነገር አልሆነም ወዮልን ከእነዚህ ከኃያላን አማልክት እጅ ማን ያድነናል? እነዚህ አማልክት ግብፃውያንን በምድረ በዳ በልዩ ልዩ መቅሰፍት የመቱ ናቸው» (መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 4፥7)

የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የሆኑት ፍልስጤማውያን እንደዚህ የሚፈሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሞገስ የሆነው ታቦት (ቃሉ) በእግዚአብሔር ቤት አገልጋይ በካህኑ ኤሊ ልጆች ዘንድ ክብርና ተገቢው ፍርሐት አልተሰጠውም ነበር። ስለዚህም የእግዚአብሔር ታቦት በጠላቶቻቸው ተማርኮ የእግዚአብሔርም ሕዝብ ለከፍተኛ ሽንፈት ተዳረገ፣ ኤሊም ከነልጆቹ ተቀሰፈ። (መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 3፥13፤ 4፥11)

ለእግዚአብሔር ታቦት የሚገባውን ክብርና ሥርዓት የማይፈፅሙትና በማይገባው ሥፍራ ከጣኦታቸው ጐን ያቆሙት ፍልስጤማውያንም በደዌና በፍርሐት ተመተዋል። (መፅሐፈ ሳሙኤል 5፥7)

## የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚያስተናግድ መንግሥት

ንጉሥ ዳዊት ሁለተኛው የእስራኤል ንጉስ ሆኖ በነብዩ ሳሙኤል በተቀባ ጊዜ በአባቱም ሆነ በሌሎች ዘንድ ከተቀሩት ወንድሞቹ ጋር የሚወዳደር ቁመናና መልክ አልነበረውም። ነገር ግን ልብን የሚያየው እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈሱን በመላክ የእስራኤል ንጉስ አድርጐ ሾመው (መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 16፥7-13)

ንጉሥ ዳዊትም ለእግዚአብሔር ቃልኪዳን ምልክት ለሆነው ለእግዚአብሔር ታቦት የገዛ ሚስቱ እስከምትንቀው ድረስ እራሱን በማዋረድ ዝማሬና ክብርን እየሰጠ የእግዚአብሔርም ክንድ ተገልጦለት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጠላቶች ሁሉ እያሸነፈ እስራኤልን ለድል አብቅቷል (መፅሐፈ ሳሙኤል 6፥3-18)

የዳዊት መንግሥት ለእግዚአብሔር ቅድሚያ የሚሰጥ፣ የእግዚአብሔርን ምሪት የሚጠይቅና ለእግዚአብሔርም ሙሉ ክብርን የሚሰጥ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከጠላቶቹ እጅ አትርፏል።

«እነዚህ ፍልስጥኤማውያንን ልምታን?» (መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 23÷2)

«ዳዊትም እግዚአብሔርን ጠየቀ እርሱም በኋላቸው ዞረህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት ግጠማቸው እንጅ አትውጣ» (መፅሐፈ ሳሙኤል ካልእ 5÷23)። «ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ ይህ በፊትህ ጥቂት ነበር። ስለባርያህም ቤት ደግሞ ለሩቅ ዘመን ተናገረህ፣ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ እስከዚህ ያደረስከኝ እኔ ማን ነኝ» (መፅሐፈ ሳሙኤል ካልእ 7÷18)

የዳዊት ሥርወ-መንግሥት (መሥመረ መንግሥት) የፅድቅና የሰላም መንግሥት ወደሆነው ወደ ክርስቶስ መንግሥት ያመላክታል።

የክርስቶስ መንግሥትም የእግዚአብሔር መንግሥት ሲሆን፤ በወንጌሉ አማካኝነት ፍፁም ፍቅርና ፍትህን ያጐናፅፋል (2ሳሙኤል 7÷16)

## የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚገዳደር መንግሥት

የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚገዳደሩ መንግሥታት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሕዝባቸውን ከጠላት የማይጠብቁ፣ የእግዚአብሔርን ቅድስና በጐ ሃሳብ የሚቃወሙና በፍሬያቸውም ሕዝባቸውን ለመለያየትና ለውድቀት ይዳርጋሉ።

የእግዚአብሔርን ምሪት ያልጠየቀው የእስራኤል ንጉስ ሳኦል በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ከነልጁ የተገደለ ሲሆን የእስራኤል ሕዝብም ንጉሥ ሳኦልንና ልጆቹን ለመሸሽና ለመበታተን በቅቷል። (መፅሐፈ ሳመኤል 31÷1-7)

የንጉስ ሰሎሞን ልጅ የሆነው ሮብአም የእግዚአብሔርን ሀሳብ በመገዳደር ኃጢአትን አብዝቶ በመሥራቱና የእግዚአብሔርን አምልኮ በማስቀረቱ ለእስራኤል ውድቀትንና መከፋፈልን ያስከተለ ሲሆን፤ ከክፉ አመራሩ የተነሳም እስራኤል ለሁለት ተከፍሏል፣ ለአያሌ ዓመታትም ለስደት ተዳርጓል። (መፅሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 12÷17-20) ዛሬም የእግዚአብሔርን ሀሳብ የሚገዳደሩ መንግሥታት ይወድቃሉ፣ ይዋረዳሉ፣ በሕዝባቸውም ይወገዛሉ።

## ማጠቃለያ

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ ሆኖ የተገለፀው የእስራኤል ሕዝብ ሲሆን በዘመኑ ከነበሩት ጠላቶች ጋር ውጊያ እንደነበረበት ሁሉ በአዲስ ኪዳንም ክርስቲያኑ ኀብረተሰብ ከዘር፣ ከነገድና ከጐሣ ጋር ሣይሆን ከጨለማው ሠራዊትና ከእርኩሣን መናፍስት ጋር ውጊያ አለበት (ኤፌሶን 6÷12)

የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር ታቦት ክብርና ሥፍራ በከለከለ ጊዜ እንደተዋረደና እንደተሸነፈ ሁሉ በአዲስ ኪዳን በዚህ ዘመናችንም ለእግዚአብሔር ልጅ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥፍራና ክብር ካልሠጠን እንወድቃለን፣ በጠላትም ዲያብሎስ እንሸነፋለን።

ስለዚህ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብና በሀገር ደረጃ ፍፁም ፍትህና እውነት ያለበትን የክርስቶስን የፍቅር መልእክት እንቀበል፣ እንመስክር፣ እንኑርበት። «እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው» (መዝሙር 32÷12)

## የእግዚአብሔር ቃል የሚያስፈልገንን ያሟላል

«የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል። የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፤ ልብንም ደስ ያሰኛል። የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፤ ዓይንንም ያበራል» (መዝሙረ ዳዊት 18÷7)

የሰብዓዊ ተፈጥሮ እንደሚያረጋግጠው ሰዎች የሚጠቀመንን ነገር እንፈልጋለን። ሌሎችን አስቀድመው ማገልገል እንደሚገባቸው ትምህርት የወሰዱት ሳይቀሩ የእራሳቸውን ፍላጐት ከማሟላት ወደኋላ አይሉም። ይህ ፍላጐት መሠታዊ የሆነው ምግብና መጠለያም ይሁን ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ሁላችንም የሚያረካንን ነገር ከመፈለግ ወደኋላ አንልም።

አንዳንድ ጊዜ የእራሳችንን ፍላጐት የማሟላት ጥረታችን ግለኛ (ራስ-ወዳድ) ያደርገናል። እራሳችንን ከመውደዳችንም የተነሳ ሌላው ነገር ምንም ላይመስለን ይችላል።

በአግባቡ ከተደረገ ለእራሳችን የሚጠቅመንን ነገር ማሟላቱ በእራሱ ክፋት የለበትም። ፍላጐታችንን ሊያሟሉልን ወደሚችሉ ሰዎች ማዘንበላችንም የተለመደ ነው።

ሰዎች በአጠቃላይ አያሌ ፍላጐቶች ያለን በመሆኑ መሠረታዊ ፍላጐታችንን ሊያሟላልን የሚችለውን የእግዚአብሔርንም ቃል ሳናስተውል እንቀራለን። ሆኖም ግን የእግዚአብሔርን ቃል አስተውለን ብናጠና እራሱ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሁሉ ሊሞላብን እንደሚፈልግና እንደሚችል እንረዳለን። «አምላኬም እንደባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል» (ፊልጵስዩስ 4÷19) «እነዚያ በሰረገላ፣ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን» (መዝሙረ ዳዊት 19÷7)

አንዳንድ ጊዜ ድካም ሊሰማንና ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን፣ በዚህ ሁኔታም እያለን

እግዚአብሔር ያለማመደንን ቃሉን የመመገብ ልማዳችንን ማቆም የለብንም ሕያውና ፈዋሽ ቃሉን መንፈሳችንና ነፍሳችን ሲመገቡ አከላታችንም ይነቃቃና አዲስ ተስፋና መነቃቃት ከእግዚአብሔር ይሆንልናል:: ደስታችን ከእኛ ሊሰረቅና ግራ ልንጋባ ተመልሰንም የእግዚአብሔርን ፅድቅ ልንሰራ እንፈልግ ይሆናል::

«የነበራችሁ ደስታ ሁሉ የት ሄደ? (ገላትያ 4÷15) ሆኖም ግን ጌታ እግዚአብሔር የሰጠን ቅዱስ ቃሉ ለሕይወታችን መብራት በመሆኑ ዘወትር እርሱን በማንበብና በማሰላሰል የከበበንን ጭጋግ እናስወግድ «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው» (መዝሙረ ዳዊት 118÷105) ዛሬ ምንድን ነው የሚያስፈልጋችሁ? ምግብ፣ መጠለያ፣ መፅናናት፣ መነቃቃት፣ ለመሻታችሁ ወደ ጌታ ሩጡ፣ ሩጡ ታገኙታላችሁ::

## በፀሎታችን ታማኝ እንሁን

ዛሬ በሁሉም ሥፍራ የእግዚአብሔር መንፈስ ሕዝቡን ለፀሎት እየጠራ ይገኛል:: ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ ለፀሎት እራሱን አላንቀሳቀሰም:: ሰዎች በየራሳቸው ጉዳይ ተጠምደው ባዝነዋል:: (Busy ሆነዋል):: አብያተክርቲያናትም ሳይቀሩ በሌሎች ፕሮግራሞች ተወጥረው ለፀሎት የሚሰጡት ጊዜ እጅግ አናሳ ወይም ምንም ሆኗል::

ጌታ ማቴዎስን ከቀራጭነት፣ ጴጥሮስን ከአሳ አጥማጅነት የጠራቸው የእርሱን መንግሥት በዚህ ምድር ላይ እንዲያሠፉ ለፀሎት ነው::

ጌታ ኢየሱስ እራሱ ቤተክርስቲያኑን «ቤቴ የፀሎት ቤት ትባላለች» ብሏል (ማቴዎስ 21÷13):: ሆኖም ግን ዛሬ የጌታን ድምፅ የሚሰማው ማን ይሆን? «መንገዱ ይህች ናት በእርስዋም ሂድ» (ኢሳይያስ 30÷21)::

አንዳንዶችም ድምፁን ቢሰሙም ለፀሎት በሚቀርቡበት ጊዜ ሕይዎታቸውን ለጌታ ከማስረከብ ይልቅ የራሳቸውን ምክንያት ያቀርባሉ:: «ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች፤ ፍፃሜዋ ግን የሞት መንገድ ነው» (ምሳሌ 14÷12)

### የእግዚአብሔር የፀጋ ተስፋ

«በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢፀልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ:: ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ:: ምድራቸውንም እፈውሳለሁ» (2ዜና መዋዕል 7÷14)

ይህ የጌታ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ተስፋ ሲሆን የሚፈፀመውም ሕዝቦቹ ቅድመ ሁኔታቸውን አሟልተው ፊቱን ሲፈልጉ ነው::

እራስን ማዋረድ አንዱ ቅድመ ሁኔታ ሲሆን ይህንን በሚገባ እንድንረዳም ጌታን እንጠይቀው:: እንደ እግዚአብሔር ቃል እራሳችንን አዋርደን በፊቱ ብንቀርብ እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ የሚገኘው አምላክ ጥያቄችንን ይመልሳል::

እግዚአብሔር ሕዝቡንና አገልጋዮቹን በፊቱ በንስኃና በኑዛዜ እንዲገኙለት ይፈልጋል:: ይህ የተስፋ ቃል በብሉይ ኪዳን የተሰጠው ለእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ተምሳሌት ለሆነው ማህበረሰብ ሲሆን የአዲስ ኪዳን ደግሞ ለክርስቲያኑ ማህበረሰብ የሚያገለግል የተስፋ ቃል ነው::

ለእግዚአብሔር ተራራውን መናድና የሸለቆውን ጉድጓድ መሙላት ምኑም አይደሉም፤ እርሱ በቃሉ ሁሉንም ማቅናት የሚችል ሁሉንም ቻይ (ኤልሻዳይ) አምላክ ነውና::

### እናንተ ለምልጃ ፀሎት ትተባበራላችሁ?

«ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የማቆምላትን ሰው በመካከላችሁ ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም» (ሕዝቅኤል 22÷30) እግዚአብሔር ዛሬም በፈረሰበት አቅጣጫ የሚቆም ሰው ይፈልጋል::

በሀገራችንም ሆነ በዓለም ዓቀፉ ደረጃ የፈረሰብን ነገር ብዙ ነው:: ህብረታችንና አንድነታችን፣ ትዳራችንና ፍቅራችን፣ መዋደዳችን፣ የመንደራችንና የከተማችን ኑሮ፣ አየራችንና አካባቢያችን ሁሉ ፈርሰዋል:: ምንም እንኳን ከውጭ መልካም ብንመስልም ብዙዎቻችን የውስጥ ሰላማችንና ወኔያችን ፈርሷል::

ስለዚህ ለግለሰብም ሆነ ለማህበረሰብ ለሀገርም ሆነ ለዓለማችን በፈረሰብን ነገር አቅጣጫ የሚፀልይ (ሰውን እግዚአሔር ይፈልጋልና እኔን ላከኝ እንበለው::

«ስለእናንተ መፀለይን በመተው እግዚአብሔርን እበድል ዘንድ ይህ ከእኔ ይራቅ» (1 ሳሙኤል 12÷23)::

ጥቂቶች ብቻ ፀሎት የለሽ ሕይዎትን ከኃጢአት ተራ ሲመድቡት በጣም ጥቂቶች ደግሞ ለሌሎች ያለመፀለይን በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን እንደመፈፀም ይቆጥሩታል፤ ላለመፀለያቸውም ንስኃ ይገቡበታል።

እኛ ደግሞ አሻሽለን ስንፍና ወይም ደንታቢስነት ስንለው ኃጢአት ለማለት ግን አንደፍርም።

ነገር ግን ኃጢአት ማለት የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መተላለፍ ከሆነ ዘንድ ፀልዩ ብሎ ጌታ በተደጋጋሚ የሰጠውን ትዕዛዝ ያለመፈፀም መተላለፍ አይደለምን? (ሉቃስ 22÷40)።

ፀሎት ከእግዚአብሔር የሚያገናኘን የእምነት እስትንፋስ (አየር) እስከሆነ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኛታችን ዋናው መለያ የፀሎት ሕይወታችን ነው።

ከእግዚአብሔር በራቅንና በተለየን ቁጥር ለሠይጣንና ለክፉ መንፈሳዊ ሠራዊቱ ስለምንጋለጥ ነፍሳችን በጠላታችን ለመበላት ትበቃለች። ብዙውን ጊዜ በግብታዊነት ሃሳባቸውን በቅዱሳን መካከል እየዞሩ ያልተቀደሰ ልምምድ የሚያስፋፉት የፀሎት ሕይወታቸው የጠወለገ ስጋውያን የሆኑ ሰዎች ናቸው።

ፀሎት ቃላትን የማሣመርና የማራቀቅ ሥራ ሣይሆን እንደ ትንሽ ብላቴና በግልፅነት ለሠማዩ አባታችን መሻታችንና ምስጋናችንን የምናቀርብበት መንፈሳዊ ንግግር ነው።

ፀሎትን የተወ ክርስቲያን ከባህር የወጣ አሳን ይመስላል፣ ሕይወትን ያጣል ለሞትም ይዳረጋል። «ሳታቋርጡ ፀልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እናንተ ነውና» አሜን። (1ተሰሎንቄ 5÷19)

## ለፀሎት የለሽ ሕይዎታችን ንስኃ እንግባ

ጌታ በተደጋጋሚ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን እንድንፀልይ ትዕዛዛቱን የሰጠን የፀሎትን አስፈላጊነት ከእኛ በበለጠ ስለሚያውቅ ነው።

በሌሎች ጉዳዩች በመጠመዳችን ብዙውን ጊዚያችንን ከፀሎት ይልቅ በመዝናናትና በወሬ ማሳለፋችንን የወንድሞቻችንና የእህቶቻችን ጉዳይ በአሉባልታ ከማስፋፋት ይልቅ በጌታ ፊት በፀሎት ባለማቅረባችን በእግዚአብሔር ፊት አሁኑኑ ንስኃ እንግባ፤ የፀሎት ሕይዎታችንም ይስተካከል። በሁሉም ሁኔታና ሥፍራ መፀለይን እንለማመድ።

## ፀሎትን ከሚያደናቅፍ ጓደኝነት እንራቅ

ከጌታ ጋር በመደበኛነት በፀሎት የምንገናኝበትን ሰዓት የሚሻማና የሚያደናቅፍን ፕሮግራም ወይም ጓደኛ እንራቅ። ከሰማያዊው የፍቅር አባታችን ለእኛ የቀረበና የሚያስብ ማንም ስለማይኖር ከእርሱ ከጌታ ጋር የሚኖረንን ቆይታ እናሻሽል።

## ፀሎትን ከሚወዱ ወገኖች ጋር እንጣበቅ

በታማኝነት በእግዚአብሔር ፊት መፀለይን ከሚወዱ ወገኖች ጋር አብዝተን እንቀራረብ። ቤት ካለንም ቤታችን ለሚፀልዩ ወገኖቻችን የተከፈተ ይሁን። ቤተክርስቲያናችንም ወደ መቅደሱ ከገባንበት ደቂቃ አንስቶ በፀሎት መንፈስ እንቆይ። ስለሰዎች ግድ ሳይለን ለአገልጋዩቹ፣ ለአባላቱና ለሀገራችን አጥብቀን እንፀልይ «በየእለቱ ሶስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ፀለየ» (ዳንኤል 6÷9)።

## የምልጃ ፀሎት ምንድን ነው?

የምልጃ ፀሎት ለአንድ ክርስቲያን እጅግ ጥልቅና ብርቱ የሆነ የአገልግሎት ዘርፍ ነው። ምልጃ ማድረግ ማለት በሁለት ወገኖች መካከል መግባት ሲሆን ይህም በሁሉን ቻይ እግዚአብሔርና በሚፀለይለት ሰው መካከል ጥያቄን ይዞ መልስ ሊሠጥ ለሚችለው እግዚአብሔር ማስታወቅ ነው።

በዘኍልቆ 16÷46 ላይ እንደምናነበው አሮን የምልጃ ፀሎቱን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በፈፀመ ጊዜ ሊመጣ ጀምሮ የነበረው መቅሰፍት ከሕዝቡ መካከል ወጣ። ከዚያ በፊት ግን ማህበሩ በኃጢአት እግዚአብሔርን በማሣዘኑ እግዚአብሔር ቁጣውን እንዳዘጋጀ ገልፆላቸው ነበር፤ «ከዚህ ማህበር መካከል ፈቀቅ በሉ እኔም በቅፅበት አጠፋቸዋለሁ» (ዘኍልቆ 16÷45)።

ከግብፅ ባርነት የወጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአቱ ምክንያት እንዳይጠፋ ሙሴ የምልጃ ፀሎትን በመፈፀሙ የእግዚአብሔር ቁጣ ቀርቶለታል። «እግዚአብሔር ሙሴን ከግብፅ ምድር ያወጣኸው ሕዝብህ ኃጢአትን ሠርተዋልና ሂድ ውረድ... ሙሴም በእግዚአብሔር በአምላኩ ፊት ፀለየ አለም ... በራስህ የማልህላቸውን ባርያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን እስራኤልንም አስብ። እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ቁጣ ራራ» (ዘፀአት 37÷7-14)

የምልጃ ፀሎት አገልጋይ ለሚያገለግለው ሕዝብ የእራሱን ሕይወት ሳይቀር አሳልፎ የሚሰጥ ርህሩህ አገልጋይ ነው። «አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከፃፍኸው መፅሐፍህ እባክህ እኔን ደምስሰኝ» (ዘፀአት 32÷32)

እግዚአብሔርም ስለባርያው ስለሙሴ የምልጃ ፀሎት ሲል ሕዝቡን ከማጥፋት እንደተመለሰ ተነግሯል፤ «ያዳናቸውንም እግዚአብሔርን ረሱ፤ እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገር» (መዝሙር 105÷23)

በየዘመናቱ የእግዚአብሔር ቁጣ ከሕዝቡ ላይ የተመለሰው በምልጃ አገልጋዮች ፀሎትና ልመና ነው፡፡ «እግዚአብሔርም አየ ፍርድም ስለሌለ ተከፋ፡፡ ሰውም እንደሌለ አየ ወደ እርሱም የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ፤ ተደነቀም» (ኢሳይያስ 59÷16)

«የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ፤ ተደነቀም» ዛሬ ይህ የእግዚአብሔር ቃል እውነት አይደለምን? ብዙዎች በኃጢአታቸው ሲቃጠሉ፣ ዓመፃና ክፋት ሲሠለጥን እየተመለከትን ባለመማለዳችን እግዚአብሔር አይደነቅምን?

«ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም» (ሕዝቅኤል 22÷30)፡፡

ውድ አንባቢዎች!

ዛሬ በመንደራችን፣ በቤተክርስቲያናችን፤ በሐገራችንና በዓለማችን ላይ የፈረሰብን ነገር አልበዛምን? ታዲያ በፈረሰው በኩል እንድንቆም እንድንማልድ የተጠራነው እኛ የልዑል እግዚአብሔር ባርያዎች ካልተነሳን ማን ሊነሳልን ነው? ምላሻችን ዛሬውኑ ይምጣ በፈረሰው በኩል ለጌታ እንቁም፡፡

## የክርስቲያን ሕይወት አዲስ ምዕራፍ

«እነሆ ይህ ከንፈሮችህን ነክቶአል፡፡ በደልህም ከአንተ ተወገደ፡፡ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ፡፡ የጌታንም ድምፅ ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል? ሲል ሰማሁ፡፡ እኔም እነሆኝ እኔን ላከኝ አልሁ፡፡ እርሱም ሂድ ይህን ሕዝብ መስማትን ትሰማላችሁ አታስተውሉምም፣ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው» (ኢሳይያስ 6÷7-9)፡፡

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ዙፋን የተመለከተና የሡራፌልንም ድምፅ የሰማ ነፍሱም በዚያ አስፈሪና አስደናቂ የእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ደንግጣ «ወዮልኝ!» ያለና ከንፈሮቹም በእግዚአብሔር ፍም በመዳበሱ ኃጢአቱ ተወግዶለት ይህንኑ መልእክት በሥልጣን ያወጀ ሰው ነበር፡፡ «ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል» በማለት ሊመሰክር የበቃው በነበረበት ዘመን የነበረውን የኃጢአት ክምችትና ርኩሰት በመረዳቱ ነበር፡፡

ዛሬም በሀገራችን ኢትዮጵያ የምናየውና የምንሰማው ነገር ሁሉ ቀድሞ ከነበረው መልካም ባህላችን እጅግ የተለየ ግፍ እየነገረንና እየሠራን እንደ እግዚአብሔር ምርጦች የእግዚአብሔር ቃል እንደፍም እሣት ሲነካን ወዮ ለእኔ! ማለት ይኖርብናል፡፡

በተለይ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃልና ቅዱስ መንፈስ የነካው፤ የተሞላና የተጠመቀ ሰው፤ አዲስ የክርስትና ሕይወት ምዕራፍ በሕይወቱ ሊታይበት ይገባል፡፡

እግዚአብሔር እኛን እርሱ ወደሚፈልገው ደረጃ ከማድረሱ በፊት በእኛ ሊከናወን የሚገባው የትህትና ሂደት አለ፡፡

ወዮ ለእኔ! ከንፈሮቼ የረከሱብኝና ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው መካከል ያለሁ!

## የማንረባ መሆናችንን እንረዳ

ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር መንፈስ ፍም ከንፈሩን ሲነካው መጀመሪያ የተረዳው የእራሱን ርኩሰትና የማይረባ እንደነበረ ነው፡፡ ወዮ ለእኔ! የሌሎችን፣ የቄሶችን፣ የጳጳሳትን፣ የወንጌላዊያንና የሌሎች አማኞችን በደል ከመቁጠር መጀመሪያ ወዮ ለእኔ! ብለን በግላችን እንናዘዝ፡፡

## እግዚአብሔር ቅርብ ነው

«ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» (ኢሳይያስ 6÷3) ምናልባት ቤተክርስቲያን ፀሎተኛ በሠፈር ዝምተኛ ላይ ላዩን ቅዱስ ለመምሰል እየሞከርን በልባችንና በስውር ስፍራና ጊዜ በኃጢአት እየተመላለስን ልንኖር እንችላለን፡፡ ግን እንወቅ ምድር ሁሉ በእግዚአብሔር የተሞላች ናትና ሰው አላየንም ብንል ጌታ ያየናልና ከክፉ፣ ከድብቅ ኃጢአታችን እንመለስ፡፡

## እንናዘዝ

ወዮ ለእኔ! በማለት ሰው የማያውቀውን ጌታና እኛ ብቻ የምናውቀውን ወይም በሰው የታወቀውን ኃጢአት ሁሉ ይዘን ወደ ቅዱስ እግዚአብሔር በንስኃ እንቅረብ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል (1ዮሐንስ 1÷7)፡፡

## በመጨረሻም የመንፈሱን እሣት እንለኩስ

የታወቀንንና ያልታወቀንን፤ ድብቁንም ሆነ ይፋውን ኃጢአት ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናዝዘን በቅዱስ እሳቱ እንዲያጠምቀን ወደ እርሱ በተስፋ እንቅረብ «እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሣት ያጠምቃችኋል» (ማቴዎስ 3÷11) አሜን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ እሳት ይውረድልን፡፡

## የእግዚአብሔር የኃይል ቃል ኪዳን (ተስፋ)

«ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (ሐዋርያት 1÷8)።

የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ እናንተ የመቀበላችሁ ጉዳይ አንድ ነገር ሲሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እናንተን መያዙ ሌላ ነገር ነው።

የዘላለም ሕይወት ሊኖራችሁ ሲችል የበዛው ሕይወት ግን ላይኖራችሁ ይችላል። በእናንተ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ መኖሩ አንድ ነገር ሲሆን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ዘንድ ሞልቶ ከእናንተ መፍሰሱ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። (ዮሐንስ 7÷38)

መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ተርፋ ወደሌሎች እንዲፈስ በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ ንስኃ ገብታችሁ ከጌታ ኢየሱስ ጋር መጣበቅ ይኖርባችኋል።

ብዙዎች መንፈስ ቅዱስ በበአለ ሀምሣ (ጴንጤቆስጤ) ዕለት ስለወረደ እነርሱ ዛሬ መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላቸው እንደሚያስፈልግ ሲናገሩ ይሰማል። ከዚህ የተነሳም ጌታ መንፈስ ቅዱስን የሚጠማ በመጥፋቱ ቤተክርስቲያን ኃይልና ጉልበት አጥታ አጋንንት ልጆቿን እየተጫወተባቸው ኃጥአንም በድፍረት በክርስቲያኖች ላይ እየተሳለቁ ይገኛሉ። እግዚአብሔር ግን የሚባላ እሣት ነው። (ዕብራውያን 12÷29)

የጌታ የተስፋ ቃል ዘላለማዊ ሲሆን ስለመንፈስ ቅዱስ እሣት በቃል የተገለፀውም በእሣት ስለሚያጠምቀው መድኃኒታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመቀደስ፣ የመፈወስ፣ የማነፅና የመሙላት የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ነው። «እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃል» (ማቴዎስ 3÷11)።

## ለምን ኃይል አጣን?

ዛሬ በዘመናችን በአብዛኞዎቹ አብያተ ክርስቲያናት በጥንተ ዘመን በሐዋርያቱ ጊዜ የነበረው ዓይነት ብርቱ የእግዚአብሔር ኃይል የጠፋው ብዙዎች ይህንን የተስፋ ኃይል ስለማይጠይቁና ስለማይጠባበቁ ነው።

ኃጢአታችንን ሳንናዘዝና ከኃጢአት ሕይወት ሳንመለስ መንፈስ ቅዱስን ለመሞላት መመኘት ፍፁም መቀለድ ይሆናል። «ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም» (ያዕቆብ 4÷3)
«ለምኑ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙአላችሁ» (ማቴዎስ 7÷7)

በእርግጥ ለእግዚአብሔር ክብርና ለመንግስቱ መስፋት ለነፍሳትም ምርኮ ጤናማ መሻት ካለን እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈሱን እየሞላን በኃይል በብርታት እንደተስፋ ቃሉ የበለጠ ታምራቶቹ በእኛ ይታያሉ (ማርቆስ 16÷18 ሐዋርያት 2÷47) (ዮሐንስ 14÷12)

## እግዚአብሔር መንፈሱን የሚሰጠው ለሚታዘዙት ነው

ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉ ሰዎች ጥቂት ብቻ የሆነበት ሌላኛው ምክንያት ብዙዎቹ ለመንፈስ ቅዱስ ባለመታዘዝ ስለሚመላለሱ ነው።

ማናችንም ብንሆን ወተትን በአሮጌና በዛገ ቆርቆሮ መጠጣት አንፈልግም፤ ነገር ግን በአዲስና በንፁህ ጣሳ ወይም ኩባያ እንጠጣዋለን። ስለዚህም አሮጌው ሰዎችን በመንፈስ ሳይሞት፤ በአሮጌ ስጋዊ ልምምዳችን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መመኘት ዘበት ነው! «ሁሉም ተፈቅዷል ሁሉም ግን አያንፅም» (1ቆሮንቶስ 6÷12) በሕይወታችን ያለ ኃጢአት ያልሆነ አመለካከትና አስተሳሰብ ቢሆን ወይም ሌላ ምክንያት ጌታ ለክብሩ እንቅፋት ከሆነበት ከእኛ እንዲወስደው በታማኝነት ጌታን እንጠይቀው።

## ማጠቃለያ

ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስና ለኃይሉ ዘወትር በመጠማት፣ በመታዘዝና በመፍቀድ የሠይጣንንና የዓለምን ውጊያ የምናሸንፍበትን ብርታትና ጉልበት ከጌታ እንቀበል። «መንፈስ ይሙላባችሁ» «የሚራቡና የሚጠሙ ይጠግባሉና» (ማቴዎስ 5÷6፤ ኤፌሶን 5÷18)።

## በንፁህ ልብ ቤተሰባችንና ቤታችን ወደጌታ ይቅረብ

«ልበ ንፁሖች ብፁዓን ናቸው። እግዚአብሔርን ያዩታልና» (ማቴዎስ 5÷8)።

በዛሬው ዓለማችን ብዙዎች መልካም የመሰሉ ሥራዎችን ሲፈፅሙ የሚታዩት የእራሳቸውን ክብርና ዝናን በመፈለግ ነው።

እግዚአብሔር ግን የሚፈልገው በንፁህ ልብ እራሳቸውን ሳይሆን እርሱን የሚያስከብሩትን አገልጋዮቹን ነው።

ለእራሳቸው ክብርና ዝና የሚያገለግሉ ሰዎች የለመዱትና የሚጠብቁት ክብርና ሙገሳ የቀረባቸው እለት ያንን በጎ ሥራ ብለው የያዙትን ነገር እርግፍ አድርገው ለባስ የከፋ ሥራና ጥፋት ይዳረጋሉ።

በንፁህ ልብ ግን ጌታን የሚጠሩና ለእርሱ ክብር በበጐ ሥራ የተሰማሩ ሁሉ ይለመልማሉ። የሰዎች አስተያየትና ሙገሳ ሳይሆን የጌታ ዘላለማዊ ቃል ያስጀመራቸውን በጐ አገልግሎት ያስፈፅማቸዋል።

## ልባችን ለእግዚአብሔር ያለውን ሥፍራ እንወቅ

የልባችን (አእምሯችን) ሁኔታ ለጌታ እጅግ ተቀዳሚው ነገር ነው። «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና (ምሳሌ 4÷23)።

ከሌሎች ጋርም የሚኖረን መንፈሳዊ ህብረት ከልባቸው ንፅህናና ቅንነት ጋር የተያያዘ መሆን ይገባዋል። «በንፁሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ፅድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል» (2ጢሞቴዎስ 2÷22)።

ንፁህ ካልሆነ ልብ የእግዚአብሔር ሥራና በጐነት በእውነት አይገለጥም፣ አይወጣም። ሰዎች ከውጭ ንግግራችንና ምላሳችን ሊያታልላቸው ይችላል። እግዚአብሔር ግን የውስጡን ማንነታችንን ሰው የሚያየውን ልባችንን ያያል። ያውቃል።

«ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል» (1 ሳሙኤል 16÷7)። ልባችን አዕምሯችንና አስተሳሰባችንን ያጠቃልላል።

እያንዳንዱን የቤተሰባችንን አባል የልብ ሀሳቡን እንዲገልፅ እናበረታታው። ከተቻለም በከለር የልብ ስዕል ላይ በመሳል እናለማምደው።

ከቤተሰባችን ጋር ዘወትር በምንፀልይበት ወቅት ልባችንን እግዚአብሄር እንዲያስተካክል ፀሎታችንን እናቅርብ።

«አቤቱ ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ፤ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ» (መዝሙር 50÷10)

እግዚአብሔር አምላካችን ዓላማው የልጆቹ ሰላምና በጐነት መሆኑን ለልጆቻችንና ለመላው ቤተሰባችን እየገለፅን ወደዚህ የእግዚአብሔር ዓላማ ሁሉም የቤተሰብ አባል እንዲደርስ የእግዚአብሔርን ፕላን (እቅድ) በተደጋጋሚ እንመስክር፤ «የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል። የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው። (መዝሙር 32÷11) «ለእናንተ የማስባትን አሳብ አውቃለሁ የሰላም አሳብ እንጅ የክፉ ነገር አይደለም። እናንተ ትጠሩኛላችሁ እኔም እሰማችኋለሁ» (ኤርሚያስ 29÷12)

## አጭር የመዳን ምክር

1. ኃጢአተኛ ስለመሆናችን ከመፅሐፍ ቅዱስ አንብበን በመረዳት ንስኃ እንግባ፣ መንገዳችንንም እናስተካክል (ሮሜ 3÷23፤ 6÷23) (ትንቢተ ኢሣይያስ 55÷7፣ 1÷18)
2. ለኃጢአታችን የተሰቀለውን፣ የሞተውንና በሶስተኛው ቀን ከሙታን የተነሳውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወታችን ጌታና አዳኝ አድርገን በእምነት እንቀበለው። (ማርቆስ 10÷33፤ ዮሐንስ 1÷12)
3. የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሚሰበክበት ማህበረ ምዕመናን ከሚገኙ ወገኖች ጋር በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ ሕብረትና አምልኮ እናድርግ። (ማቴዎስ 28÷19፤ 2 ቆሮንቶስ (3÷14)

## ዓለም ዓቀፍ የፀሎት ርዕሶችና ምሥክርነቶች

### *ለክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) እንፀልይ*

በዓለም ዙሪያ የዘላለም ሕይወትንና ሰላምን የሚያስገኘውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሚያሰራጩ የክርስቲያን የመገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) አገልግሎት አብዝተን እንፀልይ። በመገናኛ ብዙኃን ወንጌሉን ሰምተው ስለሚድኑትም አያሌ ነፍሳት ጌታን እናመስግን።

በሀገራችን ኢትዮጵያም ታላቅ የወንጌል ማዳረስ ይፈፅም የነበረውንና በደርግ መንግሥት ተወርሶ አሁንም ላለው መንግሥት ሥራ ብቻ የተመደበውን የሬዲዮ ጣቢያ ጌታ እንዲመልስልን እንማፀነው።

### *በዓለም ዙሪያ በእምነታቸው ለሚሰደዱ ወገኖቻችን ምልጃ እናቅርብ*

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል በማመናቸውና በመመስከራቸው በከፍተኛ ስደትና ስቃይ እስራትና ግድያ ላይ ላሉት ወገኖቻችን በተለይም በቻይና፣ በሰሜን ኮርያ፣ በሲሪላንካ፣ በኢንዶኖዥያ፣ በኤርትራና በሕንድ ለሚገኙት በደረሰባቸው መከራ ወደኋላ እንዳያፈገፍጉ ለጌታ ምልጃ እናቅርብላቸው።

### *በበጐና በንፁህ ልብ የፍቅር ሥራ እንሰማራ*

በሩቅ ምሥራቅ የደረሰው የሱናሚ የባህር ማዕበልና ሞገድ አደጋ ሰለባዎችን ለማዳን በተሠማሩት የክርስቲያን የበጐ አድራጐት መልዕክተኞች የፍቅር ሥራ የተነሣ ከዓለም ከፍተኛው የሙስሊም ቁጥር ያለባት ሀገር ኢንዶኔዥያ ሙስሊሞች አመለካከት እጅግ ተቀይሯል።

ከሱናሚ አደጋ በፊት ለክርስትናና ለምዕራቡ ዓለም የነበረው 26 በመቶ ድጋፍ ከአደጋው በኋላ ክርስቲያኖች ባሳዩት የፍቅር ሥራ ወደ 65 በመቶ አድጓል።

ጌታ እግዚአብሔርን በልጆቹ መካከል ስለገለጠው የፍቅር ሥራ ፍሬ እጅግ እናመስግነው።

«በፀሎት በቆማችሁ ጊዜ... በማንም አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት» (ማርቆስ 11÷25)

## ማሣሰቢያ ለአንባቢዎቻችን

በየጊዜው ስለምትገልፁልን የፀሎት ድጋፍ፣ የሚበረታታ አስተያየቶችና የገንዘብ ስጦታ ሁሉ ከልብ ልናመሰግናችሁ እንወዳለን።

ካለብን የጊዜና የአቅም ችግር የተነሳ ለሁላችሁም መልስ ለመመለስ ባለመቻላችን በዚሁ ዓምድ ላይ አድናቆታችንን እንገልፃለን።

ለአገልግሎቱ መቀጠልም የምታሳዩትን የፍቅር ስጦታ፣ የፀሎትና የምክር አገልግሎታችሁን አሁንም እንድትቀጥሉ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃችኋለን።

## *የአንባቢያን ደብዳቤዎች*

መንፈሳዊ መነቃቃት የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሂደት በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ጋዜጣ አንብቤያለሁ ጌታ ይባርካችሁ። በጣም ጥሩ ዝግጅት ነው። ቅዱሳንን ባሉበት ቦታ የሚያበረታታና የሚያሳድግ መንፈሳዊ ብርታትን የሚሰጥ ፀጋ ስጦታና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በተመለከተ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ጥሩ ትምህርት እየሰጣችሁ በመንፈሳዊ ሕይወትም እያሳደጋችሁ መቆየታችሁን አይቼአለሁ። በርቱ!!

*ማቴዎስ ዋና*
*ጋሞ ጐፋ*

የምፅዐቱ የምሥራች አገልግሎት ጋዜጣ የደህንነትና የሕይወት መልዕክት የያዘ በግልና በጋራ ለሚያነቡ፣ ለሚያስተምሩ፣ ለሚሰብኩ፣ ለመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ለፀሎት ጊዜ፣ ለደስታ፣ ለሐዘን ጊዜያት ለመፅናናት ታላቅ መለኮታዊ ሥራን የገለፀ በመሆኑ እጅግ ደስ ብሎኛል።

*ቄስ ሞላ ጐጃም*
*አዲስ አበባ*

ያለፉ እትሞችንና ተጨማሪ ዝርዝር ጥያቄያችሁን በመልዕክት ሣጥን ቁጥር አድራሻው ላይ ለሚገኘው ለዋናው አሳታሚ አሜሪካን መፃፍ ትችላላችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ ይጠብቃችሁ፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ፤ ይራራላችሁ፤ እግዚአብሔር ፊቱን ይመልስላችሁ ሰላሙንም ይስጣችሁ አሜን።

**የምፅዐቱ የምሥራች**

*የወንጌል መነቃቃት የትርጉም አገልግሎት*
*ትርጉምና ቅንብር:- አደፍርስ ሀብቴ መካሻ*
*አስተባባሪ:- ፋንታዬ ግርማ*
*አማካሪ:- ሠፋኒት አክሊሉ*
*አሳታሚ:- ሪክ ካርማይል*
*በወንጌል አማኞች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የሚካሄድና*
*ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግል የወንጌል አገልግሎት።*
*የስልክ ቁጥር 190612*
*የ.ፓ.ሣ.ቁ 8986*
*አዲስ አበባ*
*ኢትዮጵያ*